# ኢትዮጵያዊ ነኝ !!

አሥራደው ( ከፈረንሳይ )



አርነት ! _ የጥቁር ምድር አርማ ፤
ልዕልና ! _ የጥቁር ክብር ማማ፤
የጥቁር ደም - የጥቁር ዘር፤
የጥቁር ብቃይ - ከጥቁር አፈር፤
አንደበት !_ የፍሰሃ ቃል፤
ፋና ወጊ !_ የጥቁር ቀንዲል፤
አብሳሪ !_ የጥቁርን ልዕልና - የጥቁርን ድል ፤
ምንጭ ! _ የሰው ልጅ ዘር ግኝት፤
ማህተም ! _ የጥቁር ሕዝብ ዕሴት፤
ማተብ ! _ የሰው ልጆች ዕምነት፤
የክርስቲያን፤ የእስላሙ፤ _ የይሁዲው ቤት፤
ኢትዮጵያዊ ነኝ ! _ ነፃነተ ደሪት ።

የዘር ሃረግ _ የማይጠልፈኝ፤
የጎሳ አጥር _ ያልከለለኝ፤
የጥላቻ ግንብ _ ያልጋረደኝ፤
የቋንቋ ገመድ _ ያላሰረኝ፤
አድርባይነት_ ያላጎበጠኝ ፤
እበላ ባይነት፤ _ ያልጠፈረኝ
የንዋይ ፍቅር _ ያላዞረኝ ፤
የሕዝብ ህመም _ የሚያመኝ፤
የወገን መከራ _ የሚያስጨንቀኝ፤
አብሮነቴ _ የሚያኮራኝ፤
ኩሩ ዜጋ! _ ኢትዮጵያዊ ነኝ !!

ጀግንነት! _ የአያት የቅድም አያት፤
ማዕዘን ! _ የፃነት ድንጋይ ሃውልት፤
ቀደምት! _ የጥቁር ሕዝብ ተምሳሌት፤

አብሮነት! _ የመቻቻል ደሴት፤
ጮራ! _ የፀሐይ ብርሃን ንጋት፤
ቡራኬ! _ የእግዚአብሔር ስጦታ ሕብስት፤
ሃውልት! _ የተስፋ ምድር ታሪካዊ ቅሪት፤
ምንጭ! _ የጥቁር ዓባይ ጅረት፤
ጥቁር አልማዝ! _ የሕብረ ብሔር ውበት፤
ኢትዮጵያዊ ነኝ! - የጥቁር ሕዝብ ጉልላት ።

እንደ አንበሳ - የማገሳ፤
በጋሻ መከቴ - በጦር ደረት የምበሳ፤
በጠፍ ጨረቃ ተጉዤ - ድል የምነሳ፤
ለጠላት!_ እንደ እሬት የምመር፤
ለወዳጅ!_ ጣፋጭ እንደማር፤
እንደኮሳ! _ የማሽር፤
እንደ እንዝርት!_ የማሾር፤
ቀናኢ! _ ለነፃነቴ፤
ሟች! _ ለቃል ለዕምነቴ፤
ኢትዮጵያዊ ነኝ !_ ብቃይ የጥቁር ዘር፤
ከጥቁር ምድር - ከጥቁር አፈር።

ዝንጉርጉር _ እንደ ነብር ፤
ነቁጥ! _ የጥቁር ሕዝብ ክብር፤
ብቃይ! _ ከጥቁር አፈር፤
የጥቁር ደም - የጥቁር ዘር፤
አርነት የጥቁር ምድር - አርማ፤
የሰው ልጅ ምንጭ - የታሪክ ማማ !
ኢትዮጵያዊ ነኝ ! _ የጥቁር ሕዝብ ተምሳሌት፤
ትናት! _ ዛሬም !_ ወደ ፊት !!

አዎ ! ኢትዮጵያዊ ነኝ !!

ኢትዮጵያዊ ነኝ !!

ኢትዮጵያዊ ነኝ !!

የነፃነት ቁንጮ የሆነች ኢትዮጵያን፤ አጥንታቸውን ከስክሰው፤ ደማቸው አፍስሰው፤ ላስረከቡን አርበኞች አያትና ቅድም አያትቶቻችን ማስታወሻ ትሁንልኝ ።

ሚያዝያ 22 ቀን 2009 ዓ.ም. ( 30/05/2017 )